DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

# የትምህርት ዓመት 2020/2021 ማሳሰቢያዎች

*ይህ መረጃ የወላጆችን/የአሳዳጊዎችን እና የDCPS ተማሪዎቻቸውን መብቶች ይዘረዝራል።*

## የ2015 የእያንዳንዱ ተማሪ ስኬታማ መሆን ድንጋጌ

ይህ ማሳሰቢያ፣ በ2015 የእያንዳንዱ ተማሪ ስኬታማ መሆን ድንጋጌ (Every Student Succeeds Act of 2015) መሠረት፣ የተማሪዎን የክፍል ውስጥ አስተማሪን ሙያዊ የብቃት ደረጃውን የመጠየቅ መብት እንዳለዎት፤ እንዲሁም በማንኛውም ጊዜ የሚከተሉትን መረጃዎች መጠየቅ ይችላሉ:

- አንድ አስተማሪ ለክፍል ደረጃዎቹ እና የትምህርት ዓይነት መስኮቹ፣ የኮሎምብያ ዲስትሪክትን ብቁነትን ወይም የፈቃድ አሰጣጥ መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለመሆኑን፣
- አንድ አስተማሪ በአስቸኳይ ጊዜ ወይም ሌሎች ጊዜያዊ ሁኔታዎች ሲገጥሙ፣ የኮሎምብያ ዲስትሪክትን ብቁነትን ወይም የፈቃድ አሰጣጥ መስፈርቶች ባስወገደ መልኩ ያስተምር እንደሆነና እንዳልሆነ፣
- አንድ አስተማሪ የሙያ የምስክር ወረቀት ባገኘበት የትምህርት መስክ ያስተምር እንደሆነና እንዳልሆነ፣
- አንድ ተማሪ አገልግሎቶች የሚሰጠው በሙያው በሚገባ ባልሠለጠኑ (paraprofessionals) (ሥልጠና ባላገኙና በሌላ አስተማሪ የስልጠና ክትትል ሥር ያሉ የአስተማሪ ረዳቶች) መሆን አለመሆናቸው እና፣ ይህ ከሆነ ደግሞ፣ የሙያ ሥልጠና የሌላቸው ረዳቶች የሙያ ደረጃቸው ምን እንደሆነ፣

እባክዎን ሁሉንም ጥያቄዎችዎን እና ማንኛውንም ሌላ ከዚህ ማሳሰቢያ ጋር ተዛማጅነት አለው የሚሉትን ጥያቄዎች፣ ለዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች በኢሜል dcps.hrdataandcompliance@dc.gov ወይም በፋክስ በ(202) 535-2483 ይላኩ።

## የተማሪ መብቶች ጥበቃ ማሻሻያ

ይህ ማስታወሻ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እና ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎችን (ለአቅመ አዳም ደርሰዋል ተብለው የተገመቱ ልጆች ወይም 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ በሆነ እድሜ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች) ዳሰሳ መጠይቆችን ስለማካሄድ እና ስለ አካላዊ ምርመራዎች/ስለ ማጣሪያዎች እና በግላዊ መረጃዎችን ለገበያ የንግድ አገልግሎቶች የመጠቀም መብቶች ይገልጻል። እነዚህ መብቶችች፣ በተማሪ መብቶች ጥበቃ ማሻሻያ (20 U.S.C. § 1232h; 34 CFR Part 98) (“PPRA”) ላይ የተብራሩ ሲሆን፣ በመረጃው ውስጥም እንዲቀርቡ ተደርገዋል። በዳሰሳ መጠይቆች ሥራ ላይ መዋል እና መረጃዎች አሰባሰብ፣ የመረጃዎቹን ውጤት ይፋ የማድረግ እና በግላዊ መረጃዎች ለንግድ፣ ለሽያጭ ወይም ለሌላ የስርጭት አገልግሎቶችን በሚመለከት DCPS ፖሊሲዎችን ነድፏል፣ ሥራ ላይም እንዲውሉ አድርጓል። በhttps://dcps.dc.gov/surveys ላይ የሚገኘው የDCPS የዳሰሳ መጠይቅ የክንውን ቀናት፣ በእያንዳንዱ የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ እና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ላይ ተመርኩዞ፣ በምሥጢር ስለሚጠበቁ የዳሰሳ መጠይቅ መረጃዎች እና በተማሪዎች ላይ ስለሚካሄዱ አካላዊ  ምርመራዎች/ማጣሪያዎች ውጤት ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና ብቁ ሆነው ለሚገኙ ተማሪዎች ያሳውቃል። አካላዊ ምርመራዎች/ማጣሪያዎች ሁሉ ልጆቻቸው እንዳይሳተፉ እና ከክንዋኔዎቹ ሁሉ እንዲላቀቁ በመግለጽ ፈርመው ውሳኔዎቻቸውን በጽሑፍ (passive consent) እንዲያቀርቡ የሚያስፈልጋቸው ወላጆች፣ አሳዳጊዎች ወይም ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች፣ ምርጫዎቻቸውን እንዲያመለክቱ DCPS ቅጾችን ያቀርባል። እንደ ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ እንደሆነ ተማሪ፣ በPPRA ሥር የሚከተሉት መብቶች ይኖርዎታል:

1. **የዳሰሳ መጠይቆች ስምምነት።** ተማሪዎች፣ በሙሉም ሆነ በከፊል በአሜሪካ የትምህርት መምሪያ (U.S. Department of Education (USDE) የገንዘብ ድጋፍ በሚካሄድበት፣ የዳሰሳ መጠይቅ፣ ትንታኔ፣ ወይም የግምገማ ፕሮግራሞች ላይ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ብቁ የሆኑ ተማሪዎች እንዲሳተፉ ከማስፈለጉ በፊት ስምምነታቸውን መግለጽ ያለባቸውና ከሚከተሉት በምስጢር የተያዙ የመረጃ ክፍሎች ውስጥ በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑትን የሚመለከት ነው:
    - የተማሪው ወይም የተማሪው ወላጅ የፖለቲካ ወገናዊነት ወይም እምነት፤
    - የተማሪው ቤተሰቦች አእምሯዊ ወይም ሥነ ልቦናዊ ችግሮች፤
    - ስለ ጾታዊነት የሚሰጥ እሴት ወይም ስለ ግብረ ሥጋ ንክኪነት አመለካከት፤
    - ህጋዊነት የሚጎለው፣ ፀረ ማኅበራዊ፣ ራስን የሚያስወነጅል ምስክርነት መስጠት (self-incriminating), ወይም ራስን የሚያዋርድ ባህርይ ማሳየት”፤
    - ቤተ ሰብአዊ የቅርብ ግንኙነቶች ያሏቸው መልስ ሰጭዎች ስለ ሌሎች ያሏቸው ወሳኝ ግምቶች፤
    - እንደ ጠበቆች፣ ዶክተሮች፣ ወይም የቤተ ክህነት ሰዎች የመሳሰሉ ሕግ የሚያውቀው እና የተቀበለው ተዛምዷዊ በምሥጢር የሚጠበቁ ግንኙነቶች፤
    - ሀይማኖታዊ ክንዋኔዎች፣ መደባዊ ግንኙነቶች፣ ወይም የተማሪው ወይም የወላጆች እምነቶች፣ እና
    - የፕሮግራም ብቁነትን ለመወሰን በሕግ ከሚያስፈልገው ሌላ።

2. **የማገድ ችሎታ።** ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች ከሚከተሉት ተማሪን ዘወትር የማገድ ወይም የማግለል እድሎች አሏቸው፤
    - በዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት መምሪያ(USDE) የገንዘብ ድጋፍ ያልተደጎመ ማንኛውም የአሰሳ መረጃ
    - አስቸኳይ ያልሆነ፣ ማንኛውም የሰውነት ማጋለጥን ወይም መብጣት መቅደድን የመሳሰሉትን የሚጠይቅ የሰውነት ምርመራ (invasive physical exam) ወይም ትምህርት ቤት ገብቶ ለመማር በትምህርት ቤት ሥራ ላይ የሚውል ወይም በወኪሉ አማካይነት የሚከናወን ወይም ከትምህርት ቤት የመገኘት ሁኔታ የተማሪን የቅርብ የጤንነት እና የሠላም ደህነት ሁኔታ ለመጠበቅ ሳይሆን (የመስማት፣ የማየት፣ እና የጀርባ አጥንት መጉበጥ (scoliosis) ማጣሪያዎች እና ማንኛውም የስቴት ሕግ ከሚጠይቀው የአካል ምርመራ/ማጣሪያ በስተቀር)፣ እና
    - ማሰባሰብን፣ ይፋ ማድረግን፣ ወይም ማናቸውም ክንዎኖች፣ ወይም ከተማሪዎች ለንግድ ሥራ ገበያ ሽያጭ፣ ወይም ለስርጭት አገልግሎት ተግባር ብቻ የተሰበሰቡ ግላዊ መረጃዎችን፣ ወይም ለስርጭት አገልግሎት የሚያካትቱ (ይህ ለማሰባሰብ፥ ለማሰራጨት፣ ወይም ከተማሪዎች የተሰበሰቡ ግላዊ መረጃዎችን፣ ለመንደፍ፣ ለመመዘን፣ ወይም ለተማሪዎች ወይም ለትምህርት ተቋማት የትምህርት ምርት ውጤቶችን ወይም አገልግሎቶችን ማቅረብን ለተሰበሰቡ ግላዊ መረጃዎች አገልግሎት ተግብር አያገለግልም።)

3. **የመመርመር መብት።** ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች፣ ጥያቄ ሲቀርብ እና ሥራ ላይ ከመዋላቸው ወይም አገልግሎት ከመጀመራቸው በፊት፣ ማጣራት ይችላሉ፤
    - ምሥጢር ተጠብቀው የተያዙ የተማሪዎች እና በሦስተኛ አካላት የተዘጋጁ አሰሳ መጠይቆች መረጃዎች፤,
    - ለማንኛውም ለገበያ ሽያጭ፣ ወይም ለሌሎች የማከፋፈያ አገልግሎቶች ግላዊ መረጃዎችን ለማሰባሰብ አገልግሎቶችን የሚውሉ መጠይቆች፣ እና
    - እንደ ሥርዓተ ትምህርት አክል መገልገያ የሆኑ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች።

መብቶቻቸው ተጥሷል ብለው የሚያምኑ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ብቁ የሆኑ ተማሪዎች በሚከተሉት አድራሻዎች የአቤቱታዎች ክስ ማቅረብ ይችላሉ፤ Family Policy Compliance Office, U.S. Department of Education, 400 Maryland Avenue, S.W., Washington, D.C. 20202.

## የወላጅ የትምህርት መብቶች እና የግል መረጃዎች የመጠበቅ መብት ድንጋጌ

የወላጅ የትምህርት መብቶች እና የግል መብት ድንጋጌ (The Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA)) ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና እድሜአቸው 18 እና ከዚህ በላይ የሆኑ ተማሪዎች ("ብቁ የሆኑ ተማሪዎች") የተማሪን የትምህርት መረጃዎች በሚመለከት የተወሰኑ መብቶች አሏቸው። ይህ የጽሁፍ ሰንድ በግልጽና በዝርዝር የተቀመጡ፡ ያለዎትን በጣም አስፈላጊ መብቶች ለማሳወቅ የቀረበ ነው:

1. **የተማሪውን የትምህርት መረጃዎች የመርመር እና የማጣራት መብት** በ45 ቀናት ውስጥ የኮሎምብያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS)፣ መረጃዎቹን ለማግኘት ጥያቄ ይደርሰዋል። ወላጆች/አሳዳጊዎች ወይም ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ለመርመር የሚፈልጉትን (ጓቸውን) መረጃዎች የሚገልጽ የጽሑፍ ጥያቄ ለትምህርት ቤቱ ርዕሠ መምህር ማቅረብ ይኖርባቸዋል። የትምህርት ቤቱ ርዕሠ መምህር ወይም ሌላ ተገቢ የሆነ የትምህርት ቤት ባለሥልጣን መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችል ሁኔታዎችን በማመቻቸት ወላጅን/አሳዳጊን ወይም ብቁ የሆነን ተማሪ መረጃዎቹ የሚመረመሩበት ጊዜ እና ቦታ ያስታውቃል ወይም የተጠየቁት መረጃዎች ከሌሉም ያስታውቃል።
2. **የተማሪውን የትምህርት ማስረጃዎች እንዲስተካከሉ የመጠየቅ መብት** ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ሆኖ የሚገኝ ተማሪ በFERPA ሥር የትምህርት ማስረጃዎቹ ትክክል አይደሉም ወይም ያሳስታሉ ወይም የተማሪውን የግል መብት ያዛባሉ ብሎ የሚያምንን የሚመለከት ነው። ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ሆነው የሚገኝ ተማሪ ለትምህርት ቤት ርእሠ መምህር፣ እንዲለወጥ ስለሚፈልጉት የትምህርት መረጃው ክፍል በትክክል በመለየት እና በማብራራት ለምንስ መለውጥ እንዳስፈለገ በግልጽ ሊጽፉ ይገባል። በወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ በሆነው ተማሪ እንደ ተጠየቀው፣ DCPS መረጃውን ላለማስተካከል ከወሰነ፣ ትምህርት ቤቱ ለወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ለሆነው ተማሪ፣ ስለ ውሳኔው በመንገር ለማስተካከል ስለተጠየቀው ጉዳይ በችሎት እንዲታይላቸው የመጠየቅ መብት እንዳላቸው ይመከራቸዋል። በፍርድ የመታየቱን የአቀራረብ ቅደም ተከተል ተጨማሪ መረጃ ለወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ሆኖ ለሚገኝ ተማሪ በፍርድ እንዲታይ ለማድረግ ያላቸው መብታቸው በሚገለጽላቸው ጊዜ እንዲያውቁ ይደረጋል።

3. **የግል መለያ የሆኑ መረጃዎች ይፋ እንዲወጡ (በጽሁፍ) የመስማማት መብት** ሲሆኑ እነዚህም የFERPA ባለሥልጣናት ያለስምምነት ይፋ ሊያወጧቸው ከሚችሏቸው በስተቀር በተማሪው የትምህርት መረጃዎች ውስጥ የሚገኙትን ነው። ለምሳሌ፣ ተማሪው ለመመዝገብ በሚፈልግበት ወይም በተመዘገበበት ትምህርት ቤት እና የተማሪውን የትምህርት መረጃዎች ይፋ ማድረግ ለተማሪው ምዝገባም ሆነ ለዝውውር ተግባር አገልግሎት በሚጠየቅበት ጊዜ DCPS ያለስምምነት ለሌላ ትምህርት ቤት ወይም ለሌላ ትምህርት ቤት ወረዳ ባለ ሥልጣናት መርጃዎቹን ይፋ ያደርጋል። በተጨማሪም፣ DCPS ህጋዊ ትምህርት ነክ ዝንባሌዎች ይኖራቸዋል ብሎ ለሚያስባቸው ባለሥልጣናት FERPA የትምህርት መረጃዎች ያስምምነት ፈቃድ ይፋ እንዲወጡ ሊያዝ ይችላል። የትምህርት ቤት ባለሥልጣን በDCPS አስተዳዳሪ፣ ሱፐር ቫይዘር፣ አስተማሪ፣ ወይም ረዳት አባል ሆኖ የተቀጠረ ሠራተኛ (የጤና ወይም የህክምና ባለሙያ እና የሕግ አስከባሪ አባል ሠራተኞችን ጭምሮ)፣ DCPS፣ ልዩ ሥራ እንዲያከናውን የተኮናተረው (እንደ የሕግ ጠበቃ፣ ኦዲተር፣ የህክምና ባለሙያ፣ ወይም ፈውስ ሰጪ (therapist) የመሳሰሉትን)፣ እንዲያከናውን የተኮናተርው ሰው ወይም ኩባንያ፣ ወይም ወላጅ/አሳዳጊ፣ ተማሪ ወይም ለምሳሌ በሥነ ሥርዓት ወይም አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም በሕጋዊ ኮሚቴ፣ ወይም ኃላፊነቱን ወይም ኃላፊነቷ ለመወጣት ለሚያገለገል ወይም ለምታገለግል ለሌላ ትምህርት ቤት ባለ ሥልጣን ሥራ የሚያግዝ ተማሪ ወይም ሌላ የበጎፈቃድ ሠራተኛ ነው። የትምህርት ቤት ባለ ሥልጣን ሙያዊ ኃላፊነቱን ወይም ኃላፊነቷን ለመወጣት የትምህርት ማስረጃዎችን ለመመርመር ከፈለገ ወይም ከፈለገች ህጋዊ ትምህርታዊ ፍላጎቶች አሉት ወይም አሏት ማለት ነው።

4. **አቤቱታ የማቅረብ መብት** ዩኤስ የትምህርት መምሪያ ከFERPA ጋር መሟላት የሚገባቸውን ጉዳዮች በሚመለከት DCPS አላሟላም ተብሎ የተከሰሰበትን ጉዳይ በሚመለከት። FERPAን የሚያስተዳድር ጽሕፈት ቤት ስም እና አድራሻ እንደሚከተለው ነው፤ Family Policy Compliance Office, U.S. Department of Education, 400 Maryland Ave. SW, Washington, DC 20202.

5. **ተማሪውን የስም ማውጫ መረጃዎች (directory information) ይፋ እንዳይወጡ የመጠበቅ መብት።** በራሱ መብት መሠረት፣ DCPS "የስም ማውጫ (directory) መረጃዎች" በአጠቃላይ ጎጂ ናቸው ተብለው የማይገመቱ ወይም የግልን መብት የማይጻረሩ መሠረታዊ መረጃዎችን በዲስትሪክቱ እና FERPA ሕግመሠረት ያለ ወላጆች/አሳዳጊዎች ወይም ብቁ የዕድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች የፈቃድ ስምምነት ይፋ ማድረግ ይችላል። ወላጆች/አሳዳጊዎች ወይም ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ከታች የተመለከተውን 'የተማሪ የስም ማውጫ (directory) መረጃዎችን እንዲሰጥ መፍቀጃ' ቅጽን በመሙላት፣ DCPSን ከላይ ከተገለጹት መረጃዎች መካከል ጎጂነት የሌላቸውን ጥቂቶቹን ወይም ሁሉንም ይፋ እዳያወጣ መከልከል ይችላሉ።

### በምርጫነት (OPTIONAL) – የተማሪ የስም ማውጫ (Directory) መረጃን አለመስጠት

DCPS ይፋ የሚያወጣውን መረጃ ለማገድ ምርጫ ሊያደረጉ ይችላሉ። ያለ እርስዎ ስምምነት DCPS ከዚህ በታች ይፋ እንዲያደርጋቸው የማይፈልጓቸው መረጃዎች ካሉ እባክዎን ምልክት ያድርጉባቸው:

- ❑ የተማሪው ስም
- ❑ የተማሪው አድራሻ
- ❑ የወላጅ/አሳዳጊ ኢሜል
- ❑ የክፍል ደረጃ
- ❑ በይፋ የታወቁ እንቅስቃሴዎች እና ስፖርቶች መካፈል
- ❑ የአትሌቲክ ቡድኖች አባላት ክብደት እና ቁመት
- ❑ ከዚህ በፊት የተማሩባቸው ትምህርት ቤቶች ስም
- ❑ የተማሪው የተወለደበት ዘመን እና የትውልድ ቦታ
- ❑ የተቀበሏቸው ዲፕሎማዎች/ሽልማቶች
- ❑ የተማረባቸው ቀናት
- ❑ የተማሪው የስል ቁጥር ዝርዝር
- ❑ የሚማርበት ትምህርት ቤት ስም

ከዚህ በታች በመፈረም፣ የሚከተሉትን አረጋግጣለሁt:

- DCPS ከላይ ምልክት ያደረኩባቸውን የሚመለከት ምንም ዓይነት መረጃን ይፋ አያደርግም፣
- ምልክት ያላደርኩባቸውን ማናቸውንም መረጃዎች፣ ከዚህ ቀጥየ DCPS ይፋ ሊያደርግ እንደሚችል ተስማምቻለሁ፣ እንዲሁም
- ይሁን እንጂ፣ DCPS አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እና በFERPA የተፈቀደ ከሆነ፣ ይህንን መረጃ ይፋ ሊያደርግ እንደሚችል ተገንዝቤአለሁ።

**የተማሪ ስም:** ____________________________________________ **የወላጅ/አሳዳጊ ስም:** __________________________________

**ፊርማ:** ________________________________________________ **ቀን:** ____________________________________________________